# *ማፈሪያዎች ሆይ! ‹‹በግድግዳው ላይ የተጻፈውን አታነቡም››?*

ከይኄይስ እውነቱ

አሻንጉሊቱ ‹ጠ/ሚኒስትር› በአሥራ አንደኛው ሰዓት ላይ አሻንጉሊት የካቢኔ አባላት መሰየሙን በተለመደው የገደል ማሚቶነት ‹አሳውቋል›፡፡

በዛሬው የግል አስተያየቴ ሦስት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ያለኝን ምልከታ፣ አሳብና ውስጣዊ ስሜት በመጠኑ ለወገኖቼ አካፍላለሁ፡፡ እነዚህም *ከዝንጀሮ ‹ቆንጆ› ምን ይመራርጡ፣ ኢትዮጵያዊነት* እና *የወያኔ ቋሚ ባሕርይ* (ባሕርይ ያልኩበት ምክንያት ከወንበዴው ተፈጥሮ /*ሥሪት ጋር* ያለውን የማይለወጥ ጠባይ ለማመልከት ነው ) ናቸው፡፡

የወቅቱን የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለሚከታተል ሰው አእምሮው ካልተለየውና ዓይነ ልቡናው ካልተደፈነ በስተቀር  ወንበዴው የወያኔ ‹ሥርዓት› ማክተሚያ ዋዜማ ላይ መሆናችን ግልጽ ነው፡፡ የማምሻውንም ዕድሜ ‹የመረቁለት› እንደ ወያኔ ኢትዮጵያ ትፍረስ የሚሉና ባልተፈጠሩ የሚሻላቸው ጥቂት ስድ አደጎች፤ ኢትዮጵያዊ ማንነት የለም ሲሉ ባደባባይ ያቀረሹ ‹የተማሩ› ደናቁርቶች፤ የሕዝብ ውክልና ሳይኖራቸው ወያኔ የሰፋላቸውን የጎሣ ከረጢት የሙጢኝ ያሉት አንዳንድ ‹ወገኖች›፤ በአዲስ የጎሣ ማንነት ፍለጋ* ኢትዮጵያዊነትን የዘነጉ ጽንፈኞች፤ እንዲሁም ቢያንስ የጋራ ባላንጣን ለማስወገድ በቂ ኅብረት መፍጠር የተሳናቸው በውስጥና በውጭ ያሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ተዋናዮች ናቸው፡፡

## *ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ*

በዚህ ቀውጢ ሰዓት ለሕዝብ አለኝታ ከመሆን ይልቅ መላው አካሉ በ‹ጋንግሪን› የተሸመደመደውን የደደቢት ሽፍታ በ‹ካቢኔ› አባልነት የተቀላቀሉት ‹አዳዲስ ፊቶች› (አዲስነታቸው በአካል መገለጣቸው እንጂ ክህደቱ የዋለ ያደረ እንደሆነ ይገመታል) ዓላማ ምን ይሆን? መቼም ‹ተአምር› ሠርተው ወያኔን በ‹ጥልቁ ሊያድሱት› አይደለም፡፡ ይህን ቆሻሻ ሥርዓት በማጽዳት ረገድ ከቀደሙት ፍርፋሪ ለቃሚዎች የሚለዩበት አንዳች ምክንያት አይኖርም፡፡ አዲሶቹ ‹አዲስ› አይደሉም እንጂ ቢሆኑ እንኳን በነተበ ጨርቅ ላይ አዲስ እራፊ መጣፍ ይሆናል፡፡ ይህም እርስ በርሳቸው እንዳይጠባበቁ ከማድረጉም በላይ ‹አዲሱ› አሮጌውን ቦጭቆት ሁለቱም ከጥቅም ውጭ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም ‹አዲሱ› አሮጌውን የማደስ ዕድል አይኖረውም፡፡ ይልቁንም አዲሶቹ ጉዶች የአስቸኳይ ጊዜ የባርነት ዓዋጁን ተከትሎ ወያኔ

---

* *ጎሣን መሠረት አድርጎ ለተፈጸመ እልቂት (የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ በሆነ ኢትዮጵያውያን ላይ ተወዳዳሪ የማይገኝለት የጅምላ ጭፍጨፋና ሌሎችም የሚዘገንኑ ሰቆቃዎች በወያኔ መዋዕለ ዘመን ተፈጽመዋል፡፡ ዝርዝሩ በሞረሽ ወገኔ ዘገባ እና በጋዜጠኛ ሙሉቀን ተስፋው መጽሐፍ በሚገባ ተመልክቷል) ህልውናን ከጥፋት ለመታደግ፣ ራስንም እንደ ወያኔ ካሉ ከጥፋት ኃይሎች ለመከላከል የመደራጀቱ ተገቢነት የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ ሆኖም ይህን ድርጅት ከታለመለት ዓላማ ውጭ ለፖለቲካ ስናውለው ግን ከወያኔና ኦነግ አንሶ መገኘት ነው፡፡ አንዳንድ ‹ምሁራን› በሚጽፏቸው አስተያየቶች እንዲህ ዓይነቱ አደረጃጀት በቅርቡ በዳያስጶራው በሚገኙ 4 የፖለቲካ ድርጅቶች የተመሠረተው ንቅናቄ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ ማቅረባቸው እጅግ የሚያሳዝንና የሚያስተዛዝብም አዝማሚያ መሆኑን ሳልጠቁም አላልፍም፡፡ የሚገኙበትን ጎሣ ለማስደሰት፣ ዓይንና ፊት አይቶ ማዳላት፣ ከመርህ ውጭ መሆን፣ ጊዜያዊውን በዘለቄታው መለወጥ እና መሸነጋገል ለማንም አይጠቅምም፡፡*

ባዘጋጀው የጊዜ መግዣና የትኩረት አቅጣጫ ማዛቢያ ተውኔት ገጸ ባሕርያት ሆነው የተመረጡ፣ ከመድረክ ጀርባ የሚገኙት የሕወሐት አለቆች የሚያዘጋጁላቸውን የተውኔት ጽሑፍ ሳያዛቡ የሚተውኑ ቋንጃቸው የተቆረጠ ባርያዎች ሆኖ ለማገልገል የተሰየሙ ስለመሆናቸው ነጋሪ አያስፈልግም። ‹አዳዲሶቹን› ተዋናዮች ለየት የሚያደርጋቸው በቍጥር በዛ ያሉቱ የ‹ፕሮፌሰርነት› ማዕርግ እና ‹ዶክትሬት ድግሪ› የተላበሱ መሆናቸው ነው። ይህ አካዳሚያዊ ማዕርግ እንደ ወያኔ አለቆች በሐሰት/በችሮታ የተገኘ ካልሆነ ማፈሪያነታቸውን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል። ይህች ኢትዮጵያ እስከ መቼ የ‹ተማሩ› ደናቁርት መጫወቻ ትሆናለች? ስም/ዝና ፍለጋ እንዳንል ሥርዓቱ የተራ ባለጌዎችና ወራዶች ስብስብ ነው። ባለቀ ሰዓት ፍርፋሪ ፍለጋም ከሆነ ይህም ከኅሊና የመፋታት ትልቅ በሽታ ነው። ቀድሞውኑ ኅሊና የት አለ እንዳትሉኝ እንጂ። አንድ ነገር ግን እንዳትዘነጉ፤ በወያኔ ‹የአይሁድ ሽንጎ› ቡራኬ ካገኛችሁበት ጊዜ ጀምሮ ሥርዓቱ ዕለት ዕለት በሚፈጽመው ወንጀል አባሪ ተባባሪ መሆናችሁን። ወያኔ ለሚሠራው ነውር ኹሉ የመሥዋዕት ፍየል እያዘጋጀ ከደሙ ንጹሕ ነኝ በሚሉ ቀጣፊዎች የተሞላ ቡድን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ‹ቆንጆዎቹን› ከነፃነት በኋላ ይመርጣል። ከዝንጀሮ ‹ቆንጆዎች› ግን ማንንም አይመርጥም። አገር አፍራሽ ዝንጀሮዎችን በሙሉ ወደ ታሪክ ገደል አሽቀንጥሮ እንደሚወረውራቸው አልጠራጠርም።

## *ጥቂት ስለ ኢትዮጵያዊነት*

- ❖ ለእኔ ኢትዮጵያዊነት የጋራ ቋንቋ ነው። በአራቱም ማዕዘናት ያለንን ዜጎች የሚያስተሳስር/የሚያዋሕድ።
- ❖ ከፈጣሪ እግዚአብሔር ጋር የተገባ ቃል ኪዳን ነው ኢትዮጵያዊነት። የልዑል እግዚአብሔር ምሳሌ የሆነው የሰላሙ ንጉሥ ሊቀ ካህን መልከ ጼዴቅ ልጆች በመሆናችን።
- ❖ ኢትዮጵያዊነት ሕይወትን የሚለውጡለት ግዙፍም ረቂቅም ህልውና ነው። ሥጋዊም መንፈሳዊም ሀብት ነው ።
- ❖ በዘመናት እምባ፣ ደም፣አጥንት የተገነባ በልብ ጽላት የተቀረፀ ቤተ መቅደስ ነው ኢትዮጵያዊነት።
- ❖ ኢትዮጵያዊነት እየተራቡ፣ እየተጠሙ፣ እየተራዙ ጭምር (በጊዜውም ያለጊዜውም) በበጎም ሆነ በክፉ ሲነሳ የሚሳሱለት የሚነዝር ስሜት ነው ።
- ❖ በዘር፣ በባህል፣ በታሪክ ሥስትዮሽ የተገመደ የጎሣ፣ የነገድ፣ የእምነት ስብስቦች እንደ ዋርካ የሚጠለሉበት በጌጥ የተንቆጠቆጠና ያሸበረቀ *ድባብ* ነው ኢትዮጵያዊነት።
- ❖ ኢትዮጵያዊነት በኅብረ መልክዕ (ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ፣ ቀይ) ያሸበረቀ ሦራ ግምጃ፣ የሰው ልጆች በሙሉ ዘር ምንጭነት ነው ።
- ❖ በአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ የታተመ ቃል ኪዳን ነው ኢትዮጵያዊነት ።

በአፍ በመጣፍም፣ ከአባት እናቶቼ፣ ከአያት ቅድመ አያቶቼ ኢትዮጵያዊነትን የተረዳኹትና የወረስኩት በዚህ መልኩ ነው። ሁለተኛ የመፈጠር ዕድል ቢኖር እንኳ ኢትዮጵያዊ ሆኖ መፈጠርን አጥብቄ የምመኘው ነው። በመሆኑም ከኢትዮጵያዊነት ውጭ ሰው እንጂ ሌላ አይደለሁም።

ከሃዲ ካልሆነ፣ ባንዳ ካልሆነ፣ ብሎርናውን ለከርሡ የሸጠ ካልሆነ፤ ባልደከመበት፣ ፈልጎና ፈቅዶ ባልሆነው የጎሣ ማንነት ተወሽቆ የንዋይና የሥልጣን ቅንዝር እረፍት የነሳው ካልሆነ … ***ኢትዮጵያዊ መልኩን አይቀይርም።*** ኢትዮጵያዊነቱን ከያዘ ስለ ጎሣ ማንነት ጠያቂ አለ ወይ? ከልካይና ፈቃጅስ አለ ወይ? ለጎሣው መለያ የሆኑትን ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ሀብቶች የማጎልበት የማዳበር መብቱን እኩልነትና የሕግ የበላይነት የነገሠበት ሥርዓት ዋስትና አይሆነውም ወይ? መዘዙ የሚመጣው ጎሣና ፖለቲካ የተገናኙ ጊዜ ነው። ሁለቱ ጨርሶ ኅብረት የላቸውም። የጎሣ ፖለቲካ በየትኛውም መልኩ ምንጊዜም (ያለምንም ልዩ ሁኔታ/exception) አግላይ ነው። ሲያልነቱን (የአገር አንድነትን በማናጋት፣ ጎሣን መሠረት ባደረገ ጅምላ ጭፍጨፋው፣ ቅጥ ባጣ ዝርፊያው፣ ቊልፍ አገራዊ ሀብትን እና ተቋማትን ባንድ ጎሣ ቊጥጥር ሥር በማድረግ ወዘተረፈ) ወያኔ በተግባር አሳይቶናል። በአገር ላይ ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ፈንጂ ከመቅበር ልዩነት የለውም። ወያኔ ‹‹ …ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች…›› በማለት ለ25 ዓመታት የነገደብን ይበቃል። እነዚህ አባባሎች በኢትዮጵያ ዓውድ ትርጉም አይሰጡኝም። አገራችንን የቤተ ሙከራ ‹አይጥ› ማድረጉ ይብቃ። ***ኢትዮጵያ በምትባል አገር ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።*** መጽሐፍ መለየትን የሚፈልግ ምኞቱን ይከተላል እንደሚለው። ከ80 በላይ የሚሆን የልዩነት አጥር እናበጅ ካላልን ለሁላችን በጎሣ ላይ ያልተመሠረተ የእኩልነት ሥርዓት ለመፍጠር በቂ መሠረቶች አሉን። ጎረቤታችን ኬንያ (ከ70 በላይ ጎሣዎች አሏት) ሕዝቡ ራሱን ኬንያዊ በማለት ነው የሚጠራው፤ ናይጀርያም (ከ300 በላይ)፣ ሕንድም (ከ2000 በላይ ጎሣዎች ይገኛሉ) እንዲሁ… ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል። ለጎሣና ነገዶች ጥበቃ ዋስትና የሚሰጥ ሌላው ጎሣ ሳይሆን ሕዝብ መክሮ ዘክሮ ተግባራዊ የሚያደርገው ሕገ መንግሥት ነው።

### *የወያኔ የማይለወጥ ባሕርይ (ቋሚ ጠባይ)*

ስለ ወያኔ ብዙ ተብሏል። ብዙዎች አሁንም ልብ ያላሉት ጉዳይ ቢኖር የማይለወጥ ባሕርይውን አለማወቅ ወይም ቢያውቁም የከንቱ ምኞት ሰለባ መሆናቸው ይመስለኛል። ወያኔ በበቀልና በቂም ተረግዞና ተወልዶ፤ ደም እየጠጣ በጥላቻ፣ በጭካኔ፣ በዘረኝነት ተኮትኩቶ ተጣሞ ያደገ፤ ማለቂያ በሌለው ቅጥፈት፣ ዝርፊያ ፣ ክህደትና ባንዳነት በተመረዘ አስተሳሰብ የጎለመሰ እኩይና እቡይ ቡድን ነው። ይህ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ያዋረደ ቡድን ማንነት እንዴት ቢነገረን ነው የሚገባን። ከእባብ እንቁላል ርግብ እንዲፈለፈል እንዴት እንጠብቃለን? ሕወሐት መለያየትን የህልውናው ዋና መሠረት አድርጎ ለዚህ መሠሪነቱ መታሰቢያ በአኖሌ ጣዖት ያቆመ ሥጋ ለበስ የአጋንንት ቡድን ነው። የእሬቻው እልቂት የሚያንገበግበን ኢትዮጵያውያን በሙሉ፣ የኦሮሞ ወገኖቼ በተለይ ይህንን የመለያየት ሐውልት ጊዜ ሳንሰጥ አመድ ዱቄት በማድረግ የወያኔን ቅስም መስበር ብቻ ሳይሆን ነፃነታችንን እናፋጥን።

ወያኔ ስስ ብልታችንን (ለኢትዮጵያ አንድነትና ለግዛት ሉዐላዊነቷ ያለንን) አውቆ ሲጫወትብን የከረመው ይበቃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባርነት በቃኝ ብሏል። ጥገና/እድሳት አልጠየቀም። ***አንድና ብቸኛ ጥያቄው የሥርዓት ለውጥ ነው።*** የነፃነት ኃይሎች ነን የምንል በውስጥም በውጭም የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ይህ የለውጥ ጥያቄ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም። የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እውነት ሕዝብን እንወክላለን ካላችሁ ያለማመንታት

አቋማችሁን ከሕዝቡ ጋር አንድ አድርጉ፡፡ ይህ ጽንፈኝነት አይደለም፡፡ ባላንጣችን መሠረቱም ጉልላቱም ሐሰት በመሆኑ ለእርቅ ለድርድር ቦታ የለውም፡፡ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ወያኔ በየጊዜው ለሚያሳየን የማስመሰያ ተውኔቶች ልባችንን በፍጹም እንዳንሰጥ፡፡ አደራ በሰማይ አደራ በምድር፡፡ ነፃነታችንን በደማችን እንዋጃለን፡፡

አንዳንድ ምሁራን በጎ በማሰብ፤ አንዳንዶችም ከፖለቲካ ትክክለኛነት አንፃር መካከለኛ የፖለቲካ አመለካከትና ፖሊሲ አራማጆች (centrist) መሆናቸውን ለማሳየት፤ አንዳንዶችም የጨነቀው እርጉዝ ያገባል በሚለው ሥጋት ጉም ዘገና ነፋስ ጐሰማ እንደሆነ እያወቁ ወያኔን ሲለማመጡ፣ የማይተኙልንን የምዕራባውያንን በር አጥብቀው ሲያንኳኩ፣ ሲማልዱ ይስተዋላል፡፡ አእምሮአቸው ይህን እንዲያደርጉ ቢያዛቸውም የልባቸው አሳብ በተቃራኒው እንደሆነ በምድር ላይ ያለው ጽድቅ በጉልህ ያሳያቸዋል፡፡ በሁለት ልብ ማነከሳችሁን አቁሙ፡፡ ኢትዮጵያ ወያኔን ተሻግራ ህልው ሆና በአንድነቷ በነፃነቷ ትቀጥላለች፡፡ ትምክህታችንም ፈጣሪና ሕዝባችን ነው፡፡ በእግዚአብሔር ዘንድ የተቆረጠውን የወያኔ ‹ሥርዓት› ህልውና ለመቀጠል በከንቱ አንድከም፡፡ በኢትዮጵያ ‹ግድግዳ› ላይ በጉልህ ቀለም የተጻፈው ይህ ነውና፡፡ ወያኔ እስከነ ‹ሕገ መንግሥቱ› መወገድ አለበት፡፡ ማስተዋሉን ያድለን፡፡

የኢትዮጵያ ትንሣኤ ልዕልናዋን ለማየት ያብቃን፡፡